# Safety Alert on Herceptin

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት አስተዳደር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1112/2019 በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት በሀገራችን ገበያ ላይ የዋሉ መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ጥራናፈዋሽነት ቅኝት በማድረግ ያረጋግጣል።

በዚህም መሰረት ባለስልጣኑ ከHoffman Roche የተባለው የመድሀኒት አምራች ተወካይበ Herceptin 440 mg batch number H5170 ላይየተጭበረበረና ተመሳስሎየተሰራ መድኃኒት በተለይም በኬንያ ሀገር እንደሚገኝ አሳውቋል።ይህ መድኃኒት በሀገራችን የተመዘገበ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ወደ ሀገራችን አልገባም።ነገር ግን በህገወጥ መልኩ ይህ መድኃኒት በሀገራችን ውስጥ ሊገኝ ስለሚችል ህብረተሠቡ ይህን አውቆ ጥንቃቄ እንዲያደርግና ይህን መድኃኒት መጠቀም እንዲያቆም ባለስልጣኑ ያሳስባል።

በተጨማሪም ህብረተሰቡም ሆነ ጤና ባለሙያዎች ስለመድኃኒቶች ጥራት ወይም ትክክለኛት ከተጠራጠሩ ለባለስልጠኑ ባዘጋጀላቸው ሪፖርት የማድረጊያ ቅፅ፣ በሞባይል ወይም ባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ በሚገኘው ሪፖርት የማድረጊያ መንገድ እንዲሁም በኢሜይል (contactefda@efda.gov.et /pharmacovigilance@efda.gov.et)ና በነፃ ስልክ መስመር 8482 ተጠቅመው ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም እንዲያሳውቁ በአክብሮት እንጠይቃለን።

# Safety Alert on Carvedilol

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1112/2019 አንቀጽ 38 በተሰተው ስልጣን መሰረት ውስጥ ተመዘግበው ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ የዋሉ መድኃኒቶችን ጥራት ደህንነት ፈዋሽነት በመከታተልና በመቆጣጠር አያይዞም ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ የህብረተሰቡን ጤና የመጠበቅ ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። ለዚህም ስራ ሀገራዊና አለማቀፋዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ይጠቀማል።

በመሆኑም ከአለምጤና ድርጅት በተገኘ መረጃ መሰረት ካርቪደንክ (ካርቪዲሎል) 25 ሚሊግራም 30 ፍሬ የሚይዝ በአርቴሳን ፋርማ ጂኤም ቢኤች ኮኬጂ ጀርመን የተመረተ አንድ ባች batch number(ቁጥር) 27374 የተመረተበት ቀን 3/5/2022 የአገልግሎት ዘመኑ የሚያበቃበት ቀን 5/5/2025) የሆነ መድኃኒት የተቀመጠለትን የላቦራቶሪ ጥራት ደረጃ የማያሟላ ከደረጃ በታች የሆነ መድኃኒት መሆኑን አረጋግጧል

ባለስልጣኑም ተጨማሪ ባካሄደው የማጣራት ስራ ይህ መድኃኒት ሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ አስመጪና አከፋፋዮች አማካኝነት ከአምራቹ ተገዝቶ ሀገር ውስጥ መከፋፈሉን አረጋግጧል። በመሆኑም ለመድኃኒቱ አስመጪና አከፋፋዮች እንዲሁም ለተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚከተሉትን ማሳሰቢያዎች ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል።

አስመጪና አከፋፋዮች

አስመጪና አከፋፋዮች የተጠቀሰውን ችግር ያለበት መድኃኒት መሸጥ አቁመው በመጋዘናቸው ለይተው በማቆየት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ እያሳሰብን በተጨማሪም ማንኛውንም በመድኃኒቱ የአቅርቦት ሰንሰለቱ ላይ የሚካሄዱ የመድኃኒቱ ስርጭት ሽያጭ ወይም አጠቃቀም ላይ ጥብቅ ክትትል በማድረግ ያገኙትን መረጃ ለባለስልጣኑ እንዲያካፍሉ እናስታውቃለን።

ህብረተሰቡ

ይህንን መድኃኒት እንዳይጠቀሙ እያሳሰብን ተጠቅመው ወይም ሌላ ግለሰብ ተጠቅሞ አላስፈላጊ የሆነ የመድኃኒት ጎጂ ባህርይ ካጋጠመ በአስቸኳይ ወደተገቢው ጤና ባለሙያ በመሄድ ህክምና ማግኘት እንደሚገባቸው እናሳስባለን።

በተጨማሪም ባለስልጣኑ ህብረተሰቡም ሆነ ጤና ባለሙያዎች የመድኃኒት ጎጂ ባህርይ ፣ አጠራጣሪና ከደረጃ በታች ወይም ህጋዊ ያልሆኑ መድኃኒቶች በሚያጋጥሟቸው ወቅት ባለስልጣኑ ባዘጋጀላቸው ሪፖርት የማድረጊያ ቅፅ፣ በሞባይል ወይም ባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ በሚገኘው ሪፖርት የማድረጊያ መንገድ እንዲሁም በኢሜይል (pharmacovigilance@efda.gov.et )ና በነፃ ስልክ መስመር 8482 ተጠቅመው ሪፖርት እንዲያደርጉና ህብረተሰቡንጥራታቸውን ባልጠበቁ መድኃኒቶች ምክንያት ከሚደርስበት አላስፈላጊ ጉዳት መከላከል እንዲያስችሉ እንጠይቃለን።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

# Safety Alert on Phenytoin







The Ethiopian Food and Drug Authority (EFDA) is alerting the public regarding the circulation of an illegal drug marketed under the name "Epidex(Phenytoin)," with batch no. 23JP/T-222 manufactured by JIPS Pharmaceutical Pvt.Ltd, India which has been detected in the Ethiopian market. The quality, safety, and efficacy of this product is unverified, making its use potentially harmful to the public.

The EFDA strongly urges the public to avoid purchasing or using this unauthorized drug. Additionally, the authority requests that healthcare professionals and public to report the presence of this product through different reporting mechanisms such as EFDA's toll-free line at 8482 or by contacting regional health bodies.

The EFDA remains committed to protecting public health and enforcing strict drug safety standards. We thank the public for their cooperation in ensuring the safety and well-being of our communities.

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY